የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፹፯
አዲስ አበባ ነሀሴ ፱ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No. 87
ADDIS ABABA, 15th August, 2019


## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፵፮/፪ሺ፲፩ ዓ.ም


የፌደራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ (ማሻሻያ)አዋጅ የወጣ አዋጅ ....................................................ገጽ ፲፩ሺ፮፻፸፫


## CONTENT

Proclamation No.1146/2019


Proclamtion for the Establishmnet of the Office of Federal Auditor General Proclamtion (amendment)........................................Page 11673


አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፵፮/፪ሺ፲፩

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻልየወጣ አዋጅ**

የፌደራላዊ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፪/፪ሺ፰ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፡

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ ቁጥር (፩) መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

፩.**አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ የፌደራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ (ማሻሻያ)አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፵፮/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**P ROCLAMATION No.1146/2019**

**PROCLAMTION TO AMEND THE ESTABLISHMENT PROCLAMATION OF THE OFFICE OF THE FEDERAL AUDITOR GENERAL**

WHERE AS, it is has become necessary to amend the establishment proclamation of the Office of the Federal Audiror General procla mation No. 982/2016;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the " Proclamtion for the Establishmnet of the Office of Federal Auditor General Proclamtion (amendment) No.1146//2019''.

**፪.<u>የማሻሻያ</u>**

የፌደራላዊ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፪/፪ሺ፰ እንደሚከተለው ተሻሽሏል:-

፩/ በአዋጁ አንቀፅ ፪ ስር ከንዑስ አንቀፅ ፮ ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀፅ ፯ ተካቶ ንዑስ አንቀፅ ፯ የነበረው ንዑስ አንቀፅ ፰ ሆኖ የተቀሩት ንዑሳን አንቀፆች እንደቅደም ተከተላቸው እስከ ንዑስ አንቀፅ ፲፩ ተሸጋሽገው እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

፯/"ድጋፍና ልዩ ድጎማ" ማለት የፌደራል መንግስት በህገ መንግስቱ መሰረት በየ አመቱ ለክልሎች የሚሰጠው የበጀት ድጎማና ልዩልዩ ድጋፎች ነው።

፪/ በአዋጁ አንቀፅ ፭ ስር ሁለት አዳዲስ ንዑሳን አንቀፆችን ንዑስ አንቀፅ (፲፮) እና ንዑስ አንቀፅ (፲፯) በማካተት ተሻሽላል።

፲፮) የፌደራል መንግስት ለክልል መንግስታት የሚሰጠውን የበጀት ድጋፍ እና ልዩ ድጎማዎችን ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል።

፲፯) መስሪያ ቤቱ በማቋቋሚያ አዋጁ አንቀፅ ፭ የተሰጠውን የድርጅቶችን ሂሳብ ኦዲት የማድረግ ስልጣኑን እና ተግባሩን በአግባቡ ለመወጣት ተጠሪነቱ ለፌደራል ዋና ኦዲተር የሆነ ራሱን የቻለ ተቋም በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ እንዲቋቋም ያደርጋል።

፫/ በስራ ላይ ያለው አዋጅ ከአንቀፅ ፱ ቀጥሎ አዲስ አንቀፅ ፲ ተካቶ አንቀፅ ፲ የነበረው አንቀፅ ፲፩ ሆኖ የተቀሩት እንደቅደም ተካተላቸው እስከ አንቀፅ ፳፭ እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

**2. <u>Amend,ment</u>**

The Establishmnet Proclamtion No.982/2016 of the Office of the Federal Auditor General is here by amended as follows:

1/Article 2 of the Proclamation is amended by adding subArticle 7 following sub Article 6 of and the rest are rearranged from sub Article 8 to sub Article 11.

7/ " Support and Special subsidies" means Budgetary support and special subsidies the Federal Government provides annually to the Regional States in accordance with the Constitution.

2 /Article 5 of the proclamation is amended by adding two new Sub Article 16 and Sub Article 17.

16) Audit or cause to be Audited accounts involving budgetary subsidies and any special grants extended by the the Federal Governmnet to the Regional States

17) In order to properly discharge its powers and duties of auditing the accounts of enterprises as provided by its establishment Proclamation Article 5(1), establish an independent institution accountable to the Office of the Federal Auditor General as per the Regulation to be enacted by the House of Peoples' Representatives.

3/.Articles 9,10,11, and 12 of the proclamation are re-ordered to Article 10,11,12 and 13 and new Article 10 has been added as follows:

**<u>አንቀፅ ፲ ደመወዝ፣አበል እና ጥቅማ ጥቅም ክፍያ</u>**

፩/የዋናው እና የምክትል ዋና ኦዲተሮች ደመወዝ እና አበል እንዲሁም ጥቅማጥቅሞች የመንግስት ሀላፊዎችን ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ለመወሰን መንግስት ባወጣው ህግ መሰረት ይወሰናል።

፪/ዋናው እና የምክትል ዋና ኦዲተሮቹ ቀደም ሲል በጡረታ ደንብ ያልተሸፈኑ ከሆነ እና በፕሮቪደንት ደንብ ውስጥ የታቀፉ ከነበሩ በዚያው ለመቀጠል መብት አላቸው።

፫/ ዋና ኦዲተሩ ከሀላፊነት ሲነሱ ከሀላፊነት የተነሱ የሀገር እና የመንግስት መሪዎች ፣ከፍተኛ የመንግስት ሀላፊዎች፣ የምክር ቤት አባላት እና ዳኞች የሚያገኟቸው መብቶችና ጥቅማ ጥቅሞችን ለመወሰን በወጣው አዋጅ መሰረት ለሚኒስትር የተፈቀደውን ጥቅማ ጥቅም ያገኛሉ።ምክትል ዋና ኦዲተሮች ለሚኒስትር ዴኤታ የተፈቀደውን ጥቅማ ጥቅም ያኛሉ።

፬/ የአዋጁ አንቀፅ ፲ (፪) እንደተሻሻለው ንዑስ አንቀፅ ፲፩ (፪) ተሰርዞ አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፪) ተተክቷል።

፪) በአዋጁ አንቀፅ ፲ (፩) እንደተሻሻለው አንቀፅ ፲፩ (፩) የተገለፀው የስራ ዘመን ሲያበቃ ዋና ኦዲተሩ እና ምክትሎቹ ለአንድ ተጨማሪ የስራ ዘመን ሊሾሙ ይችላሉ። ነገር ግን በማንኛውም ሁኔታ ከሁለት ዙር በላይ ሊያገለግሉ አይችሉም።

**Article 10. <u>Salary,Allowance and Benefits</u>**

1/The salary,allowances and other benefits of the Auditor General and the Deputy Auditor Generals shall be determined in accordance with the law issued to provide for the salary and benefits of Government Officials.

2/ If the the Auditor General and the Deputy Auditor Generals are not previously covered by Public Penssion they shall have discretionary right to remain in the provident fund scheme to which they are beneficiary

3/ Out going Auditor General shall be entitled to the benefits to the benefits granted to a Minister, in accordance with the proclamation issued to provide for the rights and benefits of out going heads of Government ,Senior Government Officials, members of the Parliament, and judges.The out going Deputy Auditor Generals shall be entitled to the benefits granted to a State Minister..

4/ Article 10(2), as amended Article 11(2) is cancled and replaced by sub Article 2.

**2)** When the tem of office referred under Article 10 (01 of this Proclamtion as amended Article Article 11(1) ends,the Federal Auditor General and his Deputies may be appointed for the another six years term.however ,the Auditor General and his Deputies shall not be allowed to serve for more than two terms .

**፫.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሀሴ ፰ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ፕሬዝዳንት**

**3. <u>Effective Date</u>**

This proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 14th Day of August 2019**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**